# 18ኛ ሳምንት

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

"ወይ አጋጣሚ!"

### ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. መሰብሰብ 2. መቀጥቀጥ 3. ማሰር 4. መርዳት

### ማጣመር

ቃላቱን ወደብዙ ቁጥር ለውጡ።

ምሳሌ፦ ወፍ → ወፎች

1. ትል 2. ጠላት 3. እግር 4. ወቅት

### ግለንባብ

#### የዳዊት ድንጋጤ



ባዩሽ የየካ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ናት። ዘወትር ከለገዳዲ ከሰል ትገዛለች። እንደተለመደው ከሰሏን ገዝታ ወደቤቷ መጣች። አንዱን ማዳበሪያ ከሰል ማዕድቤት አስቀመጠች። በመቀጠል ዳዊትን "ደክሞኛል፤ እባክህ ቡና አፍላልኝ" አለችው። ዳዊትም፣ "እሺ እማዬ" አለና እሳት ሊያያይዝ የከሰል ማዳበሪያውን ፈታ።

⋆⋆⋆"ዳዊት ምን የሚያጋጥመው ይመስላችኋል?"⋆⋆⋆

"እማዬ! ኧረ እማዬ! የዛሬውስ ከሰል ሙሉውን ጊንጥ ብቻ ነው!" አላት። "ወይኔ ልጄን! ነደፉህ?" ብላ ከተኛችበት ዘላ ተነሳች። "አይ! የሳይንስ መምህራችን ጊንጦች መርዛማና ጎጂ ነፍሳት እንደሆኑ አስተምረውናል" አላት። እሷም፣ "ጐበዝ የኔ ልጅ! ቆይ፣ ከሰሉን በሌላ እቃ እንገልብጥና ተጠንቅቀን እንግደላቸው" አለችው።

## 2ኛ ቀን


### አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎችን በትክክል በቃላችሁ መልሱ::**

1. ጊንጥ ምን አይነት ነፍሳት ነች?
2. ባለታሪኮቹ እነማን ናቸው?
3. ቡና ሊያፈላ የነበረው ማን ነው?
4. ባዩሽ የደከማት ለምንድን ነው?
5. ባዩሽ የምትኖረው የት ነው?

### ቃላት

**ክቦቹን በተገቢ ቃላት አሟሉ::**




### መፃፍ

**ለተሰመረባቸው ቃላት ተመሳሳያቸውን ጻፉ::**

1. እባብ በሰውነት ላይ መርዙን ይረጫል::
2. አንዳንድ የዱር እንስሳት ሰውን ይጎዳሉ::
3. እባቡ እንዲሞት ራስ ራሱን ይቀጠቀጣል::
4. ዘንዶ ጠላቱን የሚያጠቃው በመዋጥ ነው::

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

"ወይ አጋጣሚ!"

### ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ፡፡

1. ጨርቅ 2. እንጨት 3. እግር 4. ሃኪም

### ማጣመርና መነጠል


የፊደላቱን ቦታ በማቀያየር ወይም በመቀነስ ቃላትን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- <u>ተቀነጣጠሰ</u> → ቀጣ፣ ጣሰ፣ ቀጠነ፣ ነጠቀ፣ ተሰነጠቀ...

1. ተበጣጠሰ 2. አተረማመሰ 3. ቀረጣጠፈ

### ግለንባብ

## አደጋ የሚያደርሱ የዱር እንስሳትና ነፍሳት



በተፈጥሯቸው የሚጠቅሙና ጉዳት የሚያደርሱ የዱር እንስሳትና ነፍሳት አሉ፡፡ ጉዳት የሚያደርሱ እንስሳትና ነፍሳት ራሳቸውን ከጠላት ለመከላከል የተለያዩ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡

***"ጉዳት የሚያደርሱ እንስሳትና ነፍሳት ሌሎችን የሚጎዱት በምን በምን ሁኔታ ይመስላችኋል"?***

ከሰውነታቸው በሚወጡ መርዛማ ነገሮች ሌሎችን ያጠቃሉ፤ እስከሞትም ያደርሳሉ:: ለምሳሌ እባብ ሲናደፍ መርዙን ይተፋል:: በዚህም ምክንያት መርዙ በሰውነት ይሰራጭና ይገድላል:: ጃርት ጠላት ሲመጣባት በሰውነቷ ላይ ያሉትን እሾሆች በመበተን ጉዳት ታደርሳለች:: ዘንዶ ጠላቱን በጅራቱ ጠምጥሞ በመያዝና በማዳከም ይውጣል:: ጊንጥና የመሳሰሉት ትናንሽ ነፍሳት ደግሞ ጠላታቸውን በመንደፍ መርዛቸውን ይረጩና ጉዳት ያደርሳሉ:: አንበሳ፣ ነብር፣ ጅብና የመሳሰሉት ሌሎችን እንስሳትና ሰዎችን በመንከስና በመብላት እስከሞት ያደርሳሉ::

## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

በመግለጫው መሠረት የእንስሳቱን ስሞች ፃፉ::

1. እሾሆቿን በመበተን ራሷን ከጠላቷ ትከላከላለች::
2. ጠላቱን በጅራቱ ጠምጥሞ በመያዝ አዳክሞ ይውጣል::
3. በመንደፍና መርዙን በመርጨት ይገድላል::
4. በመንከስ፣ ጉሮሮ በማነቅና በመቧጨር ይገድላል::

### ቃላት

በምሳሌው መሠረት ሥሩ::

ምሳሌ፦ ዋጠ ብለን መዋጥ ካልን

1. ገደለ
2. ነከሰ
3. ነደፈ
4. በላ
5. ቆረጠ

### መፃፍ

በምሳሌው መሠረት መድቡ::

| በመንከስ የሚያጠቁ | በመዋጥ የሚያጠቁ | በመንደፍ የሚያጠቁ |
|---|---|---|
| አንበሳ | ዘንዶ | እባብ |

# 19ኛ ሣምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

“ሁሉም ሙሉ፤ ሁሉም ዝግጁ!”

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ጥራጥሬ 2. ቅመማቅመም 3. ፍራፍሬ 4. ቅጠላቅጠል

### መነጠል

መነሻ ፊደሉን ከቃሉ ነጥላችሁ ፃፉ።

ምሳሌ፦ አቀረበ → አ - ቀረበ

1. አጠጣ
2. አበላ
3. አደረሰ
4. አበሰለ
5. አደረቀ

### ግለንባብ

“አሳን መብላት በብልሃት”



ዘሃራና ጓደኞቿ ወደ ባህርዳር ከተማ ለጉብኝት ሄዱ። ከተማዋ በአሳ ምርት የታወቀች ናት። በየሆቴሉ የአሳ ምግቦች:- አሳዱለት፣ አሳጉላሽ፣ አሳኮተሌት፣ አሳጥብስና የመሳሰሉት ተዘጋጅተው ይቀርባሉ። ዘሃራና ጓደኞቿም እንደየፍላጎታቸው ከአሳ ምግቦች መርጠው መመገብ ጀመሩ። አየለች ያዘዘችው አሳጥብስ ነበር። ስትበላ የሆነ ነገር ጉንጯን ጠቅ አደረጋት።

⋆⋆⋆“አየለችን ጉንጯን የወጋት ምን ይመስላችኋል?”⋆⋆⋆

“ወይኔ!” አለች:: “ምነው?” አለቻት ዘሃራ:: “ጉንጬን ወጋኝ!” “አይ አየለች! ‘አሳን መብላት በብልሃት’ ሲባል አልሰማሽም? በይ አሁንም ቀጫጭን አጥንቶች ስለሚኖሩት ተጠንቀቀሽ ብዪ” ብላ አመጋገቡን አሳየቻት::

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎቹን በፅሁፍ መልሱ::**

1. “አሳን መብላት በብልሃት” ማለት ምን ማለት ነው?
2. የአየለችን ጉንጭ የወጋው ምንድን ነው?
3. የማታውቁትን ምግብ ከመመገባችሁ በፊት ምን ማድረግ አለባችሁ?

### ቃላት

**በምሳሌው መሠረት ቃላት መስርቱ::**

ምሳሌ፦ ፈፀመ → ተፈፀመ

1. አዘጋጀ 2. ጀመረ 3. ረሳ 4. ሰማ 5. ፈጠረ

### መፃፍ

**ከፍራፍሬ ዓይነቶች አንዱን ምረጡና እንዴት እንደሚበላ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::**

ምሳሌ፦ ብርቱካን ይታጠባል፤ ይላጣል (በቢላዋ ይቆረጣል)፤ ይበላል::


## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

“ሁሉም ሙሉ፤ ሁሉም ዝግጁ!”

### ቃላት

ክቦቹን በተገቢ ቃላት አሟሉ::




### ማጣመር


በምሳሌው መሠረት ቃላት መስርቱ::

ምሳሌ፦ ከካ → ተከካ

1. ለቀመ 2. ዘራ 3. አጠበ 4. ጨመረ 5. አጠረ

### ግለንባብ

## አተር



አተር ከጥራጥሬ እህሎች ይመደባል:: በእሸትነቱ ተፈልፍሎ ይበላል:: ከደረቀ በኋላ ለምግብነት ይውላል:: የደረቀው አተር ለወጥ ሲዘጋጅ በመጀመሪያ አፈሩንና ድንጋዩን፣ ሌሎችንም ቆሻሻዎች ለመለየት ይለቀማል:: ከዚያ በኋላ ይታጠብና ይደርቃል፤ በመቀጠል ይቆላል፤ ይከካል::

⋆⋆⋆“አተር ከተከካ በኋላ ምን ይደረጋል?”⋆⋆⋆

የተከካው አተር እንደገና በነፋስ ይዘራል፣ በደንብ ይበጠራል:: ከዚህ በኋላ እንደየአቆላሉ ብስለት ክክ ወይም ተፈጭቶ ሽሮ ይሆናል:: ሰዎች የሽሮውን ጣዕም ለመጨመር ነጭ ሽንኩርት፣ ዝንጅብል፣ ነጭቅመም፣ በሶብላና የመሳሰሉትን ቅመሞች ከሽሮው ክክ ጋር ቀላቅለው ያስፈጫሉ:: ይህም ሽሮወጡን እንዲጣፍጥ ያደርገዋል::

## 4ኛ ቀን


### አንብቦ መረዳት

**ጥያቄዎችን በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ::**

1. ከአተር ሽሮ ለማዘጋጀት ምን ምን ማድረግ ያስፈልጋል?
   በመጀመሪያ ______፣______፣ _____፣ _____ በመጨረሻ _____

### ቃላት

**በምሳሌው መሠረት ክቦችን አሟሉ::**




### መፃፍ

**በምሳሌው መሠረት አሟልታችሁ ፃፉ::**

ምሳሌ፡ አተር በሰፌድ ይነፈሳል::

1. አተር በወፍጮ
2. አተር በብረት ምጣድ
3. አተር በውሃ
4. የአተር ክክ በነፋስ
5. የአተር እሸት በእጅ

## 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ



### የምግብ ዝግጅት ባለሙያ

## ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ

ምሳሌ፦ ብረትድስት → ብረትድስት ወጥ ለመስራት ያገለግላል፡፡

1. መጥበሻ 2. ማማሰያ 3. ማንኪያ 4. ቢላዋ

## ማጣመር

ፊደላቱን አጣምራችሁ ቃላት መስርቱ፡፡

| | |
|---|---|
| ምሳሌ፦ ዘ-ጋ → ዘጋ | ምሳሌ፦ ዘ - ጋ - ጋ → ዘጋጋ |
| 1. ቆ - ረ - ሰ | 1. ቆ - ራ - ረ - ሰ |
| 2. ቀ - ነ - ሰ | 2. ቀ - ና - ነ - ሰ |

## ግለንባብ

### ጤናዬና ቤተሰቦቿ



ጤናዬና ባለቤቷ የመንግስት ሠራተኞች ናቸው፡፡ በትዳር ዘመናቸው ሁለት ልጆች ወልደዋል፡፡ በእነጤናዬ ቤተሰብ ለወንድና ለሴት ተብሎ የተለየ የሥራ ክፍፍል የለም፡፡ እለቱ ቅዳሜ ነበር፡፡ ጤናዬ ወደገበያ ስትሄድ ባለቤቷ አቶ ጥግነህ ደግሞ እንጀራ ለመጋገር በዝግጅት ላይ ነበር፡፡

ሊጡን እንዳሰፋ የግቢው በር ተንኳኳ:: በሩን ለመክፈት እየሮጠ ሄደ:: “ውይ! ጤናዬ አንቺ ነሽ እንዴ?” ብሎ የያዘችውን ዕቃ ተቀበላት:: ተያይዘው ወደቤት ገቡ:: በዚህ መሃል ያሰፋው ሊጥ ትዝ አለው:: “ውይ! ውይ!” እያለ ወደ ማዕድቤት ሮጠ::

***“አቶ ጥግነህ ምን የሚያጋጥመው ይመስላችኋል?”***

ቶሎ ብሎ አክንባሎውን ከፈተ:: እንጀራው አርሯል፤ ደነገጠ:: ዞር አለና መሰቅሰቂያ አነሳ:: የእንጀራውን ጠርዝ በመሰቅሰቂያው ሰቀሰቀው ፤ ቢቆራረስም እንደምንም ለቀቀለት:: ከዚያ በኋላ እሳቱን ቀነሰውና በተደጋጋሚ ምጣዱን በጎመን ዘር አሰሰው:: ሊጥም አሰፋበት፤ ትንሽ ቆይቶ ከፈተው:: ያልተቆረሰ እንጀራ አወጣ:: ሳቅ አለ::

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት መልሱ::

1. አቶ ጥግነህ እንጀራው ያረረበት ለምንድን ነው?
2. አቶ ጥግነህ እንጀራው ሲያርበት ምን አደረገ?
3. ከእነጤናዬ ቤተሰብ ምን እንማራለን?

### ቃላት

በምሳሌው መሠረት ጻፉ::

ምሳሌ፦ እንጀራ → ይጋገራል::

1. ወጥ 2. ጥብስ 3. ዳቦ 4. ጠላ 5. ጠጅ

### መፃፍ

ዓረፍተነገር ሥሩ::


1. ሰቀሰቀ 2. አሰሰ 3. ቆረሰ 4. አረረ

## 3ኛ ቀን



### ማዳመጥ

## የምግብ ዝግጅት ባለሙያ



### ቃላት

የሚከተሉት ቁሶች ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ ለመምህራችሁ ግለፁ::

1. ምጣድ  2. አክንባሎ  3. መሰቅሰቂያ  4. ማማሰያ



### ማጣመር

ቃላቱን ወደብዙ ቁጥር ለውጡ::

ምሳሌ፦ ብርጭቆ → ብርጭቆዎች

1. ኩባያ  2. ስኒ  3. ሹካ  4. ማንኪያ



### ግለንባብ

## የምግብና የመጠጥ ቁሶች



የምግብና የመጠጥ ቁሶች እንደየአገልግሎታቸው ይለያያሉ:: ለምሳሌ ዝርግ ሳህን፣ መሶብና ትሪ ለእንጀራና ለዳቦ ማቅረቢያ ያገለግላሉ::

***"ጎድጓዳ ሳህንና ዘመናዊ ሽክላድስት ለምን ለምን ይጠቀማሉ?"***

ጎድጓዳ ሳህንና ዘመናዊ የሸክላ ድስት ለሥጋ፣ ለአትክልት፣ ለዶሮ ወጥ ማቅረቢያ ያገለግላሉ። ሹካና ማንኪያ ደግሞ ለፓስታና ለመኮረኒ እንዲሁም ለአትክልት መመገቢያ ይጠቅማሉ። ለመጠጥ ማቅረቢያ ደግሞ ስኒዎችን፣ ብርጭቆዎችንና ኩባያዎችን መጠቀም እንችላለን። የሻይ ስኒዎች ሻይ ለመጠጫ፣ የቡና ስኒዎች ቡና ለመጠጫ ያገለግላሉ። ብርጭቆዎች ለስላሳና ውሃ የመሳሰሉት ይጠጣባቸዋል። ኩባያዎች ደግሞ ለወተት፣ ለአጥሚትና ለሾርባ መጠጫነት ያገለግላሉ።

## 4ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት በጽሑፍ መልሱ።

1. በስዕሉ ላይ ያሉ እቃዎችን ዘርዝራችሁ ፃፉ።
2. ፓስታና መኮረኒ ለመብላት ምን ምን ዕቃዎች ያስፈልጋሉ?
3. ቡና በምን ይጠጣል?
4. ውሃ በምን ይጠጣል?
5. እንጀራ በምን ይቀርባል?

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ጠበሰ  2. ቀቀለ  3. ጨለፈ  4. ከተፈ

### መፃፍ

የቃላቱን ቦታ በማስተካከል ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፦ ጧት፣ በላሁ፣ መኮረኒ → መኮረኒ ጧት በላሁ።

1. ዶሮወጥ፣ ቀረበልኝ፣ ለምሳ → ____________
2. ሻይ፣ ጠጣሁ፣ በሻይ ስኒ → ____________
3. እንጀራ፣ በላሁ፣ በትሪ → ____________

# 21ኛ ሣምንት

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



"ታላላቆቻችሁን አክብሩ"

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ፡፡

ምሳሌ፦ ራበው → ጀማል ራበው፡፡

1. አዘኑ    2. ተሸከሙ    3. አሳየች    4. ረዳ

### ማጣመር

ቃላቱን በምሳሌው መሠረት በአሉታ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፦ ሰጠ → አልሰጠም፡፡

1. ተቀበለ    3. ታመመ    2. ታዘዘ    4. ያዘ

### ግለንባብ

#### መስጠትና መቀበል



አሸናፊ፣ ዘመናይና ዘቢባ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ አንድ ቀን ለእረፍት እንደወጡ፣ ዘቢባ "ዶሮ እንቁላል ይጥላል?" ብላ ጠየቀቻቸው፡፡

***"ዘቢባ ጥያቄውን ስታቀርብ አሸናፊ ምን የሚል ይመስላችኋል?"***

አሸናፊም “አሁን ይሄ ጥያቄ ነው?” ብሎ ሳቀባት:: ዘመናይም “አንተ ደግሞ ሁልጊዜ ራስህን ከፍ አድርገህ ታያለህ!” አለችው:: አሸናፊም “አይ! ማየት ሳይሆን እንቁላል የማይጥል ዶሮ ያለ ይመስል፣ ገርሞኝ እኮ ነው” አለ:: ዘመናይም “ይኸውልህ መልሱ ዶሮ እንቁላል ሊጥልም ላይጥልም ይችላል ነው:: ምክንያቱም ሴትዶሮ እንጂ ወንድዶሮ እንቁላል አይጥልም” አለችው:: ዘቢባም “ተመልከት ሁልጊዜ አውቃለሁ አትበል:: እውቀትህን ለሌሎች መስጠት ብቻ ሳይሆን መቀበልንም ተማር” በማለት ዘመናይን አቅፋ ሳመቻት::

## 2ኛ ቀን

### አንብቦ መረዳት

ለጥያቄዎቹ በጽሑፍ መልስ ስጡ::

1. መስጠትና መቀበል ሲባል ምን ይመስላችኋል?
2. ዘመናይ አሸናፊን የተቆጣችው ለምንድን ነው?
3. ዘቢባ ዘመናይን አቅፋ የሳመቻት ለምንድን ነው?

### ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ::

ምሳሌ፦ ሸኘ → ጀማል አዛውንቱን ሸኘ::

1. ተቀበለ 2. ሮጠ 3. ተሸከመ 4. መለሰ

### መፃፍ

ለጥያቄው በጽሑፍ መልስ ስጡ::

1. እናንተ በእድሜ የገፉ አዛውንት ቢገጥሟችሁ በምን በምን ታግዟቸዋላችሁ? በዝርዝር ፃፉ::

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

ታላላቆቻችሁን አክብሩ

### መነጠል

የመጀመሪያውን ፊደል ነጥላችሁ ፃፉ::

ምሳሌ፦ ተሰጠ → ተ - ሰጠ

1. ተወደደ   2. ተቀጣ   3. ተከመረ   4. ተሰደበ

### ግለንባብ

#### የመልካም ስነምግባር መገለጫዎች

ሀቀኝነት፣ ሰዎችን ማክበርና ታማኝነት የመልካም ሥነምግባር መገለጫዎች ናቸው:: ሀቀኝነት ሲባል እውነትን መናገር፣ በእውነት መስራት፣ አለመዋሸት ማለት ነው::

⋆⋆⋆"ታማኝነት ማለት ምን ማለት ነው?"⋆⋆⋆

ታማኝነት ደግሞ የተሰጠን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት፣ አደራን ተቀብሎ በአግባቡ መያዝ፣ የሰውን ንብረት ካልተፈቀደ በስተቀር አለመንካት፣ አለመስረቅና የመሳሰሉትን ድርጊቶች አለመፈፀም ናቸው:: ሰዎችን ማክበር ሲባል ደግሞ አለመሳደብ፣ ለትልልቆች ቅድሚያ መስጠት፣ መታዘዝ፣ ጓደኛን መውደድ፣ ከራስ ይልቅ ለሰዎች ማሰብን ያጠቃልላል::

## 4ኛ ቀን

## አንብቦ መረዳት

በምሳሌው መሠረት ቃላቱን መድቡ።

| | | |
|---|---|---|
| መስረቅ | እውነት መናገር | መዋሸት |
| ለራስ ቅድሚያ መስጠት | አለመታዘዝ | ታማኝነት |
| መምከር | ሰውን ማክበር | መሳደብ |
| ሀቀኝነት | | |

| | ጥሩ ስነምግባር | ጥሩ ያልሆነ ስነምግባር |
|---|---|---|
| ምሳሌ፡- | እውነት መናገር | መስረቅ |

## ቃላት

ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. ሸለመ
2. ወደደ
3. ነካ
4. መከረ
5. ዋሸ
6. ሠረቀ

## መፃፍ

የቃላቱን ቅደምተከተል በማስተካከል ዓረፍተነገሩን አስተካክላችሁ ፃፉ።

1. መምህራንን እወዳቸዋለሁ በጣም
2. አዛውንቱን ረዳኋቸው በሥራ
3. ርዕሰ መምህራችን ሰበሰቡን ዛሬ
4. ተሸከሙ እቃ አባባ
5. አባባን አገዝኳቸው ሮጬ

## 22ኛ ሣምንት

### 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ



### ሃላፊነትን መቀበል

## ቃላት

በቃላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩ።

1. የሥራ ድርሻ 2. ማገዝ 3. ሃላፊነት 4. መቀበል

## ማጣመር

ሀ. ቃላቱን አጣምራችሁ ፃፉ

ምሳሌ፦ ሥነ + ምግባር → ሥነምግባር

1. ሥነ + ህይወት 2. ሥነ + ጥበብ 3. ሥነ + ፍጥረት

ለ. ፊደላቱን አጣምራችሁ ቃላቱን ተናገሩ።

1. ሰ - ን - ደ - ቅ - ዓ - ላ - ማ 2. መ - ከ - ባ - በ - ር

## ግለንባብ

### የግርማ ጥፋት



"እማዬ! ኧረ እማዬ!" ሰብለ ተጣራች። "እርፋችሁ አትበሉም? ምን ያስለፈልፍሻል?" አሏት እናታቸው። "ይሄ ግርማ፣ የራሱን ምግብ ጨርሶ የእኔን ይበላል" እያለች አለቀሰች። "ኧረ እማ! አውቃ ነው፤ ውሸቷን ነው። የራሴን ምግብ እየበላሁ ነው" አላቸው። እናታቸውም ከጓዳ እየሮጡ መጡ። የግርማ ምግብ አልቋል።